# ቁጥር ፩

## በለንደን የደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ወጠምሻ ቦዲ ጋርድስ በአገልግሎት ጊዜ በቤተ ክርስቲያኗ በር ላይ በማቆም ቀዳሚ ሆነች።

በአውሮጳ ቀደምትነት ያላት የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተቋቋመች ከ36 ዓመት በላይ አስቆጥራለች። ይህች በጥቂት ምዕመናን በትንሽ አዳራሽ የተጀመረች ቤተ ክርስቲያን ብዙ መሰናክሎችን አልፋ ዛሬ አድጋ ሰፍታ ፤ ምዕመናኑ የራሳቸውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ገዝተው በሳምንት በአማካኝ 700 ሕዝብ ዘወትር እሁድ ይገለገልባታል። ከሆሣዕና ቀን ጀምሮ ግን የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ወጠምሻ ቦዲ ጋርድስ በአገልግሎት ጊዜ በቤተ ክርስቲያኗ በር ላይ በማቆም ፤ በድጋሚ የቀደምትነት ሥፍራ በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አስመዝግባለች። ምንም እንኳ ከሆሣዕና አንድ ሳምንት በፊት በአውደ ምሕረቱ ላይ ቦዲ ጋርድስ በቤተ ክርስቲያኗ በር ላይ እንደሚቆሙ የተነገረ ቢሆንም በሥነ ምግባር ለታነጸው ኢትዮጵያዊ ድርጊቱ ውርደት በመሆኑ እጅግ ብዙን ክርስቲያን ያስከፋ ነበር። እነዚህ በምሽት ጊዜ በብዛት በዲስኮ ቤት ወይም በመጠጥ ቤት በር ላይ ቆመው በስካርና በሌላም ስሜት ተገፋፍተው ከሥነ ሥርዓት ውጭ የሆኑ ሰዎችን የሚጠብቁ ዘበኞች ፤ የሚያስፈራሩ ኃይሎችን ፈርቶ ከሀገር ተሰዶ ለመጣው ኢትዮጵያዊ ለሆነው ወገናችን ማቆም ሥርዓት የሌለው ሕዝብ አድርጎ ማሳየት በመሆኑ በድርጊቱ ስሜቱ ያልተጎዳ የለም።

እነዚህን ለማቆም ያስፈለገበት ምክንያት ተብሎ ከተሰጠው ሰንካላ ምክንያት አንዱ ፤ ቤተ ክርስቲያኑ ሲሞላ ሰዎች ካልገባን ብለው ካስቸገሩ ለመከልከል ተብሎ ነው ይላሉ። ይህንን ያህል ዓመት ስንኖር ቤተ ክርስቲያን እንዳትገቡ የሚል ዘበኛ አስፈልጎ አያውቅም ነበር። በዓሉን አስመልክቶ በረከት ሊቀበል የሚመጣ ሕዝብ ሌሎች ቦታዎች ላይ እንደሚታየው ዓይነት ባህርይ ፤ በጉልበት ካልገባሁ ብሎ ፀብ ሲፈጥር ሰምተን አይተን አናውቅም አስተናጋጆቹ ትህትና ባልተሞላው አነጋገር በማመናጨቅ የመጡትን ካላስቀየሙ በስተቀር። ሥርዓት ለማስከበር ጥሩ ባሕርይ ያላቸውና ምዕመናኑን በደንብ የሚያውቁ በበር ላይ ቆመው በትህትናና በፈገግታ እባካችሁ ሞልቷል ወደ ድንኳን ግቡ ቢሉ ፤ ምዕመናኑ ደስ ብሏቸው ትዕዛዙን ይፈጽማሉ። ነገር ግን እንደ ሀገራችን ቀበሌ ጠባቂዎች ወይም የሆስፒታል ዘበኞች ዐይን እያጉረጠረጡ ጋጠ ወጥ በሆነ አነጋገር ከመደባደብ ባልተለየ ስሜት ከተቀበሉ ማንም ሰው ይቀየማል ወደ መጥፎ ግጭትም ሊሄድ ይችላል። ደግሞ በእነዚህ ዐበይት በዓላት የሚመጡ ምዕመናን ብዙ ጊዜ በነገሮች አለመመቻቸት የማይመጡ ስለሆነ እንደዚህ ዓይነት ያልተለመደ ሁኔታ ሲያዩ ጥሩ ዓይነት ስሜት አይኖራቸውም። ስለዚህ የሚያስፈልገው እንደቀድሞው ሥርዓት ያላቸውና ትሑት የሆኑ አስተናጋጆችን በር ላይ ማቆም ጥሩ መፍትሔ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ የተሰጠው ምክንያት ደግሞ ፖሊስ በግብጽ ሀገር በኮፕቲክ የክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ የደረሰው ዐይነት ጥቃት በዚህ በለንደን ሊፈጸም ይችላል ብሎ በሳሰበው መሠረት ነው የሚል ነው። በመሠረቱ ይኼ ጭራሽ የማይዋጥ ምክንያት ነው። ሽብርተኞቹ ግብጻውያን ናቸው ቢባል

የሚያጠቁት የኮፐቲክ እምነት ተከታዮችን እንጂ ከኬላው ክርስቲያኖች ነጥለው ኢትዮጵያውያኑን የሚያጠቁበት ምንም ምክንያት የለም። ጥላቻ ቢኖራቸው ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ነው ስለዚህ መንግሥታዊ ተቋም ያጠቃሉ እንጂ የእምነት ድርጅት የሚያጠቁበት ምንም ምክንያት የለም። ደግሞ የእንግሊዝ ሕዝብን እናስቆጣ ብለው ቢያጠቁ ፤ የአንገሊካን ቤተ ክርስቲያንን እንጂ ሌላ እንደኛ ተሰዶ የመጣውን ሕዝብ አይደለም። አለበለዚያ የሃይማኖት ጦርነት ተነሣ ማለት። እንዲያው ማሳሰቢያው ደረሰ ቢባል እንኳ በበሩ ላይ የቆሙት 2 ሰዎች ከምንም ሊያስጥሉ አይችሉም ምክኒያቱም መሣሪያ የያዘ ሰው ቢያዩ እነርሱ የራሳቸውን ሕይወት ለማዳን ከመሮጥ በስተቀር ምንም ሊያደርጉ አይችሉም። አያድርስና እንዲህ ዐይነት ሁኔታ ቢፈጠር የአካባቢው ፖሊሶች ብቻ ናቸው ሁኔውን ሊቆጣጠሩ የሚችሉት። ይሁን እንጂ እስከ አሁን ድረስ በዚህ የክርስቲያን ሀገር ላይ ከላይ የተገለጸው ዐይነት ክስተት እስከ አሁን አልተፈጠረም ወደፊትም አይፈጠርም ብለን ተስፋ እናድርጋለን። ስለዚህ ይህ ምክንያት ቦዲ ጋርድስ ለማቆም በቂ አይደለም።

በሦስተኛ ደረጃ የቀረበው አንዳንድ ምዕመናን ሊረብሹ ይችላሉ ከዚያም አልፈው በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ (ሰ.ጉ.አ)አባላት ላይ ኃይል ሊጠቀሙ ይችላሉ በሚል ነው። እንዲህ ዓይነቱ በኃይል መጠበቅማ በአፍሪካ መሪዎች የሚታይ ነው። እንግዲህ በእውነት በቅንነት የእግዚአብሔርን ቤት እናገለግላለን ካልን የመረጠንን ሕዝብ በእንደዚህ ዓይነት የፍርሐት ስሜት መምራት የለብንም። ማንም እዚህ ሥርዓት ባለው ሀገር ላይ እንዲህ ያደርጋል ተብሎ አይጠበቅም። ቢሆን እንኳ በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ላይ የነበሩትን ክርስቲያኖች ላይ የደረሰውን መከራ አስበን ለበረከት ፣ መስዋዕትነት ለመቀበል መዘጋጀት ነበረብን ዘበኛ ከማቆም ይልቅ። ለቦዲ ጋርድስ መቆም ዋናው ምክንያት ይህ በሦስተኛ ደረጃ የተጠቀሰው ይመስለል። ምክንያቱም እነዚህ ቦዲ ጋርድስ መቆም የጀመሩት በበዓለ ሆሣዕና የአሠራርና የሥነ ሥርዓት ጉድለት አለ ብለው ጥያቄ ካቀረቡት መካከል ዲያቆን ድርሻዬን ሌሊት ለአገልግሎት ሲሄድ ከበር እንዳይገባ ከመለሱት በኋላ ነው። በምንም መልኩ ይሁን የዐቢይ ጾምን ሱባዔ አንድ ላይ ሲያገለግል የሰነበተን አገልጋይ በተለይ በዚህ ታላቅ በዓል ቀን ቀጥሎም የሰሙነ ሕማማት ሳምንትና የታላቁን ፋሲካ በዓልን እንዳያከብር መከልከል ለሌላው ሰው ስሜት ደንታ አለመስጠትና ከቂመኝነት የመነጨ ኢክርስቲያናዊ ድርጊት ነው። ቤተ ክርስቲያኒቷ በሌላት ገንዘብ እነዚህን ቦዲ ጋርድስ ከማቆም ይልቅ ፤ችግር አለ ብለው ከጠየቁት ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ችግሩን በውይይት መፍታት አይሻልም ነበርን? አሁንም ይህ ያለው ቅራኔ እንደ መ/ቅዱሳችን ቃል ችግሩን መፍታትና ከቂም በቀል የራቀ ግልጽ አሠራርን አስፍኖ መሥራት የተሻለ ነው።

ለመሆኑ እነዚህ ችግር አለ ብለው አቤቱታ ያቀረቡ የረጅም ዘመን አግልጋዮች ጥያቄያቸው ከቤተ ክርስቲያኗ ሕግ አኳያ ትክክለኛ ነው ወይ? እያንዳንዳቸውን ተራ በተራ ከሕጉ አኳያ ለማብራራት እሞክራለሁ። አብዛኛው ምዕመናን ሕግ መኖሩንም ቢያውቅም በቅርቡ አግኝቶ ያላነበበው ስለሆነ ፤ እዚህ ድኅረ ገጽ ላይ ይኸው አውጥተነዋል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችን ሕግ ምን እንደሆነ ምዕመናን አውቃችሁ ሥርዓቷ እንዲከበር የማድረግ ኃላፊነት አለባችሁ፦
http://ethiopianorthodox.org/biography/constitution.pdf

አንዳንዶች ሕጉ አይሠራም ወይም ሙሉ አይደለም እያሉ የተለያየ ምክንያት ቢሰጡም ፤ ሕጉ በሚያዘው መሠረት እስካልተሻሻለ ድረስ ቤተ ክርስቲያኗ የምትመራው ከዚህ በላይ በተደነገገው ሕግ ነው። ነገር ግን ከዚህ ውጭ ቢሠራ በሕግ መንገድም ያስጠይቃል። አሁን ተፈጠረ ለተባለው ችግርና ወደፊት የሚፈጠሩ አለ መግባባት የዚህ ውጤት ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

1ኛ/ ወደ 60 የምንጠጋ ሰዎች ፊርመን አቤቱታ አስገብተን በሕጉ መሠረት ስብሰባ አልተጠራንም ለጥያቄያችንም መልስ አላገኘንም። እንዲያውም የቤተ ክርስቲያኗ ሰላም የሚነሡ ተብለን ዛቻ እና ግልምጫ ነው የቀረን የሚል ነው።

የቤተ ክርስቲያኗ መተዳደሪያ ደንብ <u>**ምዕራፍ 8 አንቀጽ 44 ቁጥር 2**</u> ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፦

## <u>*2. ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ*</u>

*ሀ) እያንዳንዱ ጉባኤ ወይም ኮሚቴ ከተገለጸው መደበኛ የስብሰባ ጊዜ ሌላ አስቸኳይ የሆነ ጉዳይ ሲ ኖር ወይም ከጉባኤው አባላት መካከል ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ አባላት ስብሰባ እንዲጠራ በ ጽሑፍ ከጠየቁ በማንኛውም ጊዜ ተጨማሪ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።*

*ለ) ከተወሰነዉ ዓመታዊ ጉባኤ ሌላ ለአስቸኳይ ስብሰባ ጠቅላላው መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲጠራ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ የሰበካዉ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉበኤ ሊጠራ ይችላል። ነገር ግን ጠቅላላዉ ጉበኤ እንዲጠራ አስፈላጊ መሆኑን በቅድሚያ በጥምር ጉባኤው ማስወሰን ይኖርበታል።*

*ሐ) ከዚህም ሌላ፤ ከጠቅላላው መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት መካከል <u>ከሃምሳ ያላነሱ ካህናትና ምእመናን</u> የቤተክርስቲያንን ጉዳይ በሚመለከት ለመምከርና ለመወያየት <u>በጽሁፍ ጠቅላላው መንፈሳዊ ጉባኤ</u> እንዲጠራላቸው የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤውን ቢጠይቁ ፤ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ በፊደል (ለ) የተጠቀሰው ሥነ ሥርዓት ተጠብቆ ጠቅላላው ጉባኤ ሊጠራ ይችላል።*

እንግዲህ ወደ 60 የሚጠጉ ሰዎች ስብሰባ ይጠራልን ወይም ጥያቄያችን ይመለስልን ካሉ ፤ የሰ.ጉ.አ መፈጸም ይኖርበታል። ይህን ካላደረገና መግባባት ከጠፋ የችግሩ መንስኤ ራሱ ሰ.ጉ.አ ነው ማለት ነው። በጥያቄያቸው መሠረት ሰብስበን አነጋግረናል የሚል ካለ ፤ ስብሰባው የተካሄደበትን አጀንዳው ከውሳኔ ጋር አያያዞ ማሳወቅ ይኖርበታል። ሰዎች ምንግዜም ተቃውሞ የሚያነሱት ሕግ ሲጣስ ነው።

**2ኛ/ በአሁኑ ወቅት ያለው የሰ.ጉ.አ የተመረጠበትን የሥራ ጊዜ ሲጨርስ ሪፖርቱን ባቀረበበት ወቅት የቤተ ክርስቲያኑ ግዝ ሊያልቅ 3 ወር እንደቀረውና ፤ ጉዳዩን እንደጀመሩት እንዲጨርሱ በጠየቁት መሠረት ፤ ምዕመናኑም ለ3 ወር እንዲቀጥሉ ፈቅደላቸው ነበር። ነገር ግን ያ 3 ወር አልፎ 2ኛ ዓመታቸው መጥቷል። በተጨማሪም ሕጉ አንድ አባል ከሁለት የምርጫ ጊዜ በላይ መሥራት አይችልም እያለ አንዳንድ አባላት ከ10 ዓመት በላይ በአባልነት እየሠሩ እንዳሉ ይነገራል።**

**የቤተ ክርስቲያኗ መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 3 አንቀጽ 10 ስለ ተመራጮች የአገልግሎት ዘመን እንዲህ ይላል፦**

1. *ለቤተክርስቲያኑ የሥራ አስፈጻሚ ጉባኤያትና ኮሚቴዎች አባልነት የተመረጡ አባላት በተመረጡበት አገልግሎት ላይ የሚቆዩት ለሦስት ዓመታት ይሆናል።*

2. *ለሦስት ዓመታት ተመርጦ ያገለገለዉ አባል መልካም ተግባሩ ታይቶ ለሁለተኛ ጊዜ በእጩነት ቀርቦ ሊመረጥ ይችላል። ይሁን እንጂ ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ሊመረጥ ስለማይችል አንዳንድ የምርጫ ጊዜ እያሳለፈ ሊመረጥ ይችላል።*

3. *በሥራ ላይ ያሉት የጉባኤያትና የኮሚቴዎች አባላት የሥራ ዘመን ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት የአዲሶቹ አባላት ምርጫ ይፈጸማል።*

**እንግዲህ ከላይ የሰፈረው ሕግ ተግባራዊ ካልሆነ የሰ.ጉ.አ አገልግሎቱን የቀጠለው ፤ ሕግ ጥሶ ነው ማለት ነው። ያለው የሰ.ጉ.አ ለረጅም ጊዜ ይቀጥል ለማለት የሚቻለው የአስመራጭ ኮሚቴ ተመርጦ አለምንም ተፅእኖ ለአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ሐሳቡን አቅርቦ ጉባኤው ካፀደቀ በኋላ እንጂ በእንዲህ ዓይነት በተደፋፋነ ሁኔታ መሆን የለበትም። አይ በትክክለኛው ነው ምርጫው የተካሄደው የሚል ከሆነ የሰ.ጉ.አ ቃለ ጉባኤውን ማሳየትና ከሕግ እንዳልወጡ ማሳየት ይኖርባቸዋል እንጂ ለተጠየቁት አለመመለስ ስህተትን እንደማመን ይቆጠራል። በዚህ ላይ ደግሞ አንድ ፕሮጀክት ሳያልቅ ኮሚቴ እንዳይወርድ የሚለው አባባል በሀገሩ ላይ ሰው እንደሌለው ያስመስላል። ፕሮጀክት ይነደፋል ኮሚቴው እስካለ ድረስ ይሠራል ፤ ካለቀ እሰይ ፤ ካላለቀ ግን የሚቀጥለው ተተክቶ ይቀጥላል። አስፈላጊ ከሆነ የቀድሞውን አባላት ምክር እየጠየቀ ይሠራል። እንኳን በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቀርቶ በሀገር ደረጃ (በምዕራቡ ዓለም) መሪዎች የረጅም ዓመታት ዕቅድ ሲነድፉ እስከዚያ ይቆያሉ ማለት አይደለም ነገር ግን እስካሉ ይሠራሉ የሚቀጥለው ደግሞ ካለበት ይቀጥላል ማለት ነው።**

በሕጉ መሠረት ለሌላ 3 ዓመት እንዲ ተመረጡ ቢባል መሐከላቸው ከ6 ዓመታት በላይ በሰ.ጉ.አ አባልነት ያገለገለ ካለ በሕጉ መሠረት ከላይ ቁጥር 2 ላይ እንደተደነገገው የግድ መተካት አለበት። አለበለዚያ ሕግ ተጥሷል ማለት ነው።

3ኛ/ ከቁጥር 2 ጥያቄ ጋር በተያያዘ በሰ.ጉ.አ ሥር ተቋቁመው የነበሩት ኮሚቴዎች በተለይ ደግሞ ዋና የሆኑት የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ (ችግሮች ሲፈጠሩ ጉዳዩን የሚያጣራ) ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ (ገንዘብ ነክና ንብረትን በተመለከተ የሚቆጣጠር) እና የካህናት ጉባኤ እንደገና መመረጥ ሲኖርባቸው ጭራሽ ሆን ተብለው ፈርሰዋል።

ከላይ የቤተ ክርስቲያኗ መተዳደሪያ ደንብ <u>ምዕራፍ 3 አንቀጽ 10 ቁጥር 1/2</u> ስለ ተመራጮች የአገልግሎት ዘመን በሚናገረው ክፍል ላይ ልክ እንደ ሰ.ጉ.አ የኮሚቴዎችም ምርጫ በተመሳሳይ መንገድ መካሄድ እንዳለበት ይገልጻል። የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴም እንደ አውሮፓ አቆጣጣር በ9/11/09 ሥራውን ማጠናቀቁንና ያለው የሰ.ጉ.አ ሕጋዊ እንዳልሆነ ገልጸው ሥራቸውን ለቀዋል። እንዲሁም ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የሚሰበሰበው የካህናት ጉባኤ ከተሰበሰበ 2 ዓመት እንደሆነውና የቁጥጥር ኮሚቴም እንደሌለ ነው። ብዙ ውሳኔዎችን ለመወሰን ፣ ሥራዎች በሚገባ እንዲከናወኑ ፣ ሐሜት እና ቅራኔን ከምዕመናኑ መሐከል ለማስወገድ ፣ እነዚህ ኮሚቴዎች በአስቸኳይ መቋቋም ነበረባቸው። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ በአስቸኳይ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ መጣራት አለበት። በደፈናው ብቻ ኮሚቴዎቹ አሉ ማለት በቂ መልስ አይደለም። አሉ ከተባለም ላለፉት 2 ዓመታት እነዚህ ኮሚቴዎች የተነጋገሩባቸውን ቃለ ጉባኤዎች ማሳየት ይኖርባቸዋል። በተለይ ደግሞ በመተዳደሪያ ደንቡ <u>ምዕራፍ 5 አንቀጽ 28 ቁጥር 1/4</u> ላይ የቤተ ክርስቲያኗ የቁጥጥር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር በሚለው ሥር፦

1. የቤተክርስቲያኑን አጠቃላይ ገቢና ወጪ በየወሩ እየተቆጣጠረ ገንዘቡ በባንክ ሒሳብ መቀመጡን ያረጋግጣል።
4. የሂሳቡ አያያዝና የንብረቱ አጠባበቅ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን በዝርዝር መዝግቦ በየሦስት ወሩ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል ይላል። ይሄ ኮሚቴ በጣም ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት ነው። ይኽን ሥራውን እየሠራ ነው ከተባለ ያው ከላይ የተገለጹትን የሠራቸውን ሪፖርት በማየት እውነቱን መገንዘብ ይቻላል። <u>የእነዚህ ኮሚቴዎች መኖር ለቤተ ክርስቲያኗ ዕድገትና ሰላም በጣም ወሳኝ ነው።</u>

4ኛ/ የቤተ ክርስቲያኗ ገንዘብ አለ አግባብ እየባከነ ነው። በሕጉ እንደታዘዘው በወቅቱ ገንዘብ ወደ ባንክ አይገባም ስለዚህ ብዛቱ ያልታወቀ ገንዘብ ጠፋ ተብሎ በአውደ ምሕረቱ ላይ የተነገረውም ከዚህ የተነሳ ነው ፤ እንዴት እንደጠፋም አልተጣራም። የሂሳብ ሪፖርትም አልቀረበም። በተጨማሪም ከረጅም ዘመን ጀምሮ የምንጠቀምበትን serial number ያለው ደረሰኝ ትተው ራሳቸው አሁን ባሳተሙት ነው የሚጠቀሙት የሚል ነው።

**በእርግጥ መጠኑ ያልታወቀ በርከት ያለ ብር መጥፋቱን የሰ.ጉ.አ በቤተ ክርስቲያኗ አውደ ምሕረት ላይ ተነግሯል ግን እንዴት ሊጠፋ እንደቻለ ስለማጣራቱ ሁኔታ የቀረበ ሪፖርት የለም። በሕጉ መሠረት (<u>ምዕራፍ 4 አንቀጽ 13 ቁጥር 13</u>) ይህን የማጣራት ኃላፊነት የተሰጠው የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ነው። ይህ የቁጥጥር ኮሚቴንም ይመለከታል። ነገር ግን እነዚህ ኮሚቴዎች ከላይ እንደተገለፀው የሉም። እንዚህ ኮሚቴዎች ባይኖሩም የሰ.ጉ.አ ተአማኒነት እንዲኖረው ጊዜያዊ አጣሪ ኮሚቴም ቢሆን አቋቁሞ ማጣራት ነበረበት።**

**በመተዳዳሪያ ደንቡ <u>ምዕራፍ 7 አንቀጽ 40 ቁጥር 2</u> ስለ ቤተ ክርስቲያኗ የገንዘብና ንብረት አያያዝ እንዲህ ይላል፦**

*2. ከእያንዳንዱ የገቢ አርዕስት የሚገኘው ገንዘብ በ24 ሰዓት ውስጥ እንደ ገቢው አይነት በተከፈተለት የባንክ ሒሳብ ገቢ ይሆናል። ወደባንክ እስከሚገባ ድረስም ገንዘቡ በጽ/ቤቱ በካዝና ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል።*

**እንግዲህ መጣራት ያለበት ምን ቦታ ላይ ተቀምጦ እንዴት ሊጠፋ እንደቻለ ፣ ለስንት ጊዜ ያህል ሳይገባ የቆየ ብር እንደሆነ ተጣርቶ ሪፖርት ለጠቅላላው ጉባኤ ሊቀርብ ይገባል። ይኽን ደግሞ ለአባላቱ ማሳወቅ ያለውን ሐሜታ ያስወግዳል። የሰ.ጉ.አ ጉዳዩን አጣርተናል ዝም ብለው ስማችንን ሲያጠፉ ነው የሚል ከሆነም ሪፖርቱንም ምዕመናኑ በጠየቁት መሠረት ማሳየት ይኖርበታል። ለማሳመንም በቤተ ክርስቲያኗ ድኅረ ገጽ ላይ በማውጣት ማስተባባል ይችላሉ።**

**የሂሳብ ሪፖርትን በተመለከተ በመተዳዳሪያ ደንቡ <u>ምዕራፍ 4 አንቀጽ 13 ቁጥር 21 እና 22</u> መሠረት ሪፖርቱን ማቅረብ ይኖርበታል። ይኽን እንደሚያደርጉ እርግጠኛ ነኝ። አባላቱም ከጽ/ቤት ሄደው በመጠየቅ መገንዘብ ይችላሉ። ነገር ግን ካልተሠራ ስህተት ነው።**

**ለአለፉት 15-20 ዓመታት በተከታታይ ቁጥር በትዕዛዝ ከኢትዮጵያ ተሠርተው የሚመጡት ደረሰኞች ቀርተው እዚሁ ሀገር በተዘጋጁ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ነው የሚሠራው የሚል ጥያቄም አለ። በተለይ እንደ ቀድሞው በሙሉ ደረሰኞቹ ተከታታይ ቁጥር ከሌላቸው ለገንዘብ መጥፋት ከፍተኛ መንገድ ይከፍታል። በእርግጥ እንደተባለው ከሆነ ብዙ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል ስለዚህ የሰ.ጉ.አ በአስቸኳይ በግልጽ ለምን መለወጥ እንዳስፈለገ ማስረዳት መቻል አለበት። ወይም ደግሞ ከዚህ ቀደም እንደሚደረገው ከኢትዮጵያ በሚመጣው ደረሰኝ እየተጠቀሙ መሆኑን በማስረዳት ያለውን ሐሜት ማክሰም አለባቸው።**

**5ኛ/ የሰ.ጉ.አ የኮሚቴ አባላት ወይም በአማካሪነት ያስጠጓቸው ግለሰቦች ዓላማቸው ይህቺን ቤተ ክርስቲያን ከሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አመራር አውጥቶ በቦርድ ለማስተዳደር ነው የሚል ነው።**

**በመሠረቱ የመተዳደሪያ ደንቡን በእንዲህ ዓይነት ሥር ነቀል ለመለወጥ ቀርቶ አንድ ዐረፍተ ነገር ለመቀየር በመተዳዳሪያ ደንቡ <u>ምዕራፍ 8 አንቀጽ 51 ቁጥር 1 እና 2</u> የውስጥ ደንቡን መሻሻል በሚናገረው መሠረት ነው፦**

*1. ዉስጠ ደንቡ እንዲሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰበካዉ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጠያቂነት **<u>በ ጥምር ጉባኤው</u>** ተጠንቶ በጠቅላላ ጉባኤዉ ከተደገፈ ሊሻሻል ይችላል።*

*2. የተሻሻለዉ ዉስጠ ደንብ ከሥራ ላይ የሚዉለዉ በአንቀጽ 50 መሠረት ለጠቅላላዉ ጉባኤ ቀር ቦ ከጸደቀ በኋላ ይሆናል።*

**ይህ ጥምር ጉባኤ የሚባለው በሰ.ጉ.አ ሥር ያሉት ኮሚቴዎች በአንድነት ሆነው የሚመሠርቱት ነው (መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 3 አንቀጽ 8 ቁጥር 8)። እንግዲህ ከላይ እንደገለጽነው በሰ.ጉ.አ ሥር የነበሩት ኮሚቴዎች በተለይ የሚመለከተው የሕግና ሥነ ሥርዓት ሁሉ ፈርሰዋል። ስለዚህ ጥቂት ሰዎች አጋጣሚውን ተጠቅመው እንዲህ ዓይነት ለውጥ ማምጣት ቢፈልጉ በምንም ዓይነት በሕግ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቢለውጡ እንዲያውም ንዑሳን ኮሚቴዎቹን ሆን ብለው ያፈረሱት ለዚህ ነው ተብሎ ሊያስወቅስ ይችላል። እንደምገምተው ከባድ ወንጀል ካልተፈጸመ በስተቀር ይህን ያደርጋሉ ብዬ አልገምትም። ከሰ.ጉ.አ አባላትም እንደተረዳሁት ማንም ቢሆን ወደ ቦርድ የመለወጥ ሃሳብ ያለው የለም ነገር ግን አንዳንድ ሙሉ ያልሆኑ ወይም ለአሠራር ያላመቹ አንቀጾችን ኮሚቴ አቋቁመን ለማሻሻል እያጠናን ነው የሚል ነው። ከላይ እንዳየነው የጥምር ኮሚቴዎች አለመኖርና የሰ.ጉ.አ ራሱ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ምንም ዓይነት አንቀጽ ሆነ ዐረፍተ ነገር በዚህ ወቅት ለመለወጥ ሕጉ አይፈቅድም። ይህ የቦርድ አመራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ሲሆን በቦርድ የሚተዳደሩ ወደ ሰ.ጉ.አ አመራር ይመጣሉ እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን ወደዚያ ልትሄድ አትችልም ሕጓም አይፈቅድም። በቅርቡም "በውጭው ያለችው ቤተ ክርስቲያን በቦርድ ወይስ በሰ.ጉ.አ ትመራ" በሚል ታሪካዊ አመጣጡንና የቦርድ አስተዳደር ጎጂነቱን የሚያስመለክት ጽሑፍ ይቀርባል።**

**6ኛ/ ሰ.ጉ.አ የተጠየቀውን ጥያቄ መልስ በመስጠት ፈንታ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ጥያቄ ያቀረቡትን ያሳድዳል ከዚያም አልፎ ቦዲ ጋርድስ በቤተ ክርስቲያኗ በር ላይ በማቆም ያልፈለጉት ምዕመንም ሆነ ካህን ገብቶ እንዳያገለግል ማድረግ ጀምረዋል። የመጀመሪያውን እርምጃ በዲያቆን ድርሻዬ ላይ የሆሣዕና ዕለት ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ገብቶ እንዳያገለግል አግደውታል።**

**በመተዳደሪያ ደንቡ <u>ምዕራፍ 5 አንቀጽ 27 ቁጥር 4 ፣7 ፣8 ፤11</u> በምዕመን ሆነ ካህን ላይ እንዲህ ዓይነት እርምጃ ማንና እንዴት እንደሚወሰድ ተገልጿል። የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ጉዳዩን መርምሮና አጣርቶ የሚሰጠው ውሳኔ በሰ.ጉ.አ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ያደርጋል እንጂ የሰ.ጉ.አ ሆነ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደሪ ማንም ላይ እርምጃ ለመውሰድ መብት የላቸውም። ይሁን እንጂ ይህ አሰራር ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም ምክንያቱም ይሄ ኮሚቴ አስቀድሞ ፈርሷል። የዚህ ኮሚቴ**

አለመኖር ለተፈጠረው ውዝግብ በሰላማዊና በፍጹም ክርስቲያናዊ መንፈስ ያለውን ችግር እንዳይወገድ ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጓል። ለማንኛውም ይህ ኮሚቴ ባይኖርም እንኳ ፤ አገልጋይ ካህንን ቀርቶ ማንንም ምዕመን ከቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ የተወሰደው አሳዛኝ እርምጃ ብዙዎችን ያስከፋ ነው። ሌላው ቢቀር የሰ.ጉ.አ ከሌሎች ሽማግሎች ጋር በመሆን ዲያቆን ድርሻዬን ሆነ ሌሎች ቅሬታ አለን ያሉት ስብሰባ ጠርቶ አጀንዳ ተይዞ ፊት ለፊት ተነጋግሮ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መድረስ ነበረበት። በሠለጠነው ዓለም የምንኖርነው ቀርቶ በሀገራችን እንኳ ሰው የማስታረቅ ሽምግልና የሚካሄደው ሁለቱንም የተጋጩትን አንድ ላይ አገናኝተው የሚሉት ካዳመጡ በኋላ ነው። ታዲያ የሁለቱንም ባሕል አለን ካልን ይህ ዓይነት አሰራር ከየት መጣ? አንዳንድ ጉዳዩ የከነከናቸው 1 ወይም 2 ሰዎች በግል እየሄዱ ያነጋገሩትን ሽማግሌዎች ተልኮ አልሰማ አለ ማለት ለጉዳዩ ትኩረት አለመስጠትና መቀለድ ነው። ዲያቆን ድርሻዬ ፊት ለፊት ተገናኝተን እንወያይ ብሎ ደጋግሞ ጠይቆ ዕድሉ እንዳልተሰጠው ተናግሯል። የሰ.ጉ.አ ደግሞ ተገናኝተን ተነጋግረናል ነገር ግን አልሰማ ስላለን ነው እርምጃ የወሰድነው ካለ ፤ ቃለ ጉባኤውን በቤተ ክርስቲያኗ ድኅረ ገጽ ላይ በማውጣት ያለውን ሐሜትና ክፍፍል እልባት እንዲያገኝ ሊያደርግ ይገባል።

ሰዎችን ሆን ብለን ከቤተ ክርስቲያን እንዳይደርሱ ማሰናከል እንደማይገባ መጽሐፍ ቅዱሳችን ያስተምረናል (ማቴ 18 ፤6-9)። እንደ መጽሐፍ ቅዱሳችን አስተምህሮ ጌታችን ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ የጠፋውን አዳም ሊፈልግ እንደመጣ (ማቴ 18፦10-14) ፤ እኛም ማባረር ሳይሆን ከዚህ ቀደም አባል የነበሩና የቀሩትን ሁሉ እየፈለግን መልሰን ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ልናመጣቸው ይገባል። በእነሱም ተመልሶ መምጣት የጠፋው ልጅ በተመለሰ ጊዜ አባቱ ፍጹም እንደ ተደሰተ (ሉቃ 15 ፤3) እኛም እንደዚያው ልንደሰት ይገባል። ለሕሊናም ደስ የሚለው ባሉት አባላት ላይ አዲስ አባላት እየጨመረ ሲሄድ ነው እንጂ ያለውን እያጡ አዲስ መሰብሰብ ብቻ አይደለም።

ቤተ ክርስቲያናችንን የምናገለግለው ከእግዚአብሔር በረከት ለማግኘት ከሆነ ፣ እንደ ቃሉ መንዝ ይኖርብናል። የሚያሳድዱችሁን መርቁ ፣ ቀኝ ጉንጭህን ሲመታህ ግራህን ስጥ ብላ የምታስተምር ቤተ ክርስቲያናችን (ማቴ 5፦38-48) ፤ ተከታይ ምዕመናኖቿን እንደ ፖለቲከኞች አታባርርም ፣ አታሳድድም። ነገር ግን ወንድምህ ቢበድልህ ሰባ ጊዜ ሰባት ይቅርታ አድርግለት (ማቴ 18 ፤21-22) የተባለውን አርአያ በማድረግ ቅሬታ ካላቸው ጋር በአስቸኳይ ተቀራርቦ በውይይት ችግሩን መፈታት ግድ ነው። አለበለዚያ የምናቀርበው መስዋዕት ሁሉ ከንቱ ነው። ቃሉ እንደሚነግረን መስዋዕት ቁርባናችንን ከማቅረባችን በፊት አስቀድመን ሄደን የተጣላነውን ልንታረቅ እንደሚገባ ራሱ ጌታችን አዞናል (ማቴ 5፦23-25)። ደግሞስ አባታችን ሆይ ብለን ስንጸልይ ........ በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል (ማቴ 6፦7-15)...... ስንል ዝም ብለን ነው የምናነበንበው ወይስ ከልባችን ቃሉን እያስተዋልን ነው።

ሰዎች ጥያቄ ሲያቀርቡ ችግሮችን በግልጽ እየተወያየን እየፈታን ከሄድን ሐሜታና ቅሬታ ይጠፋል። እንዲሁም የመንደር አሉባልታ ወሬ ሁሉ በየድኅረ ገጹ ብቅ ባላለ ነበር። ሁሉ ነገር በግልጽ ከተሠራ ፤

ሕጉን ተከትለን ከሠራን ፤ አካሄዳችንን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ካደረግን ቤተ ክርስቲያናችን የበለጠ እንደምታድግ ጥርጥር የለኝም። ከላይ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ከቤተ ክርስቲያኗ የውስጥ መተዳደሪያ አኳያ አግባብ ያላቸው ስለሆነ ሳይዘገይ በአስቸኳይ በሚቀጥሉት 2-3 ሳምንታቶች መልስ ሊሰጥባቸው ይገባል። የበለጠ ግልጽነት እንዲኖርም የሰ.ጉ.አ ማብራሪያ በቤተ ክርስቲያኗ ድኅረ ገጽ ላይ በማውጣት ሰላም በአስቸኳይ እንዲሰፍን ማድረግ ይኖርበታል። በተለይ ደግሞ በቤተ ክርስቲያኗ ደጃፍ ላይ የሚቆሙ ቦዲ ጋርድስ በአስቸኳይ ሊወገዱ ይገባል። ነገር ግን ለተነሡት ጥያቄዎች መልስ አለመስጠት ስህተትን ማመን ወይም ደግሞ ማን ይነካኛል ባይነት ስለሚሆን እና እንዲሁም ከሃይማኖት ተቋም የማይጠበቅ ስለሆነ የበለጠ ምዕመናን በሰ.ጉ.አ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ስለዚህ በአስቸኳይ ያለንን ልዩነት አስወግደን በፍቅር ፣ በአንድነት ቤተ ክርስቲያናችን እንድናገለግልና እንድናሳድግ እግዚአብሔር አምላክ በበረከቱ ይጎብኘን።

ተከታዩን ጽሑፍ ሰ.ጉ.አ የሚሰጠውን ምላሽ አይተን ፤ ለተነሱት ጥያቄዎች መፍትሔ ካልተገኘ በተከታታይ ጽሑፎች ያሉትን ችግሮች የበለጠ ምዕመናኑ እንዲያውቁት እናደርጋለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።

በእደ ማርያም እጅጉ
ሚያዚያ 2003